
# የውይይት መምሪያ ለቤተሰቦች

Reading Is Fundamental
until every child reads




**ኮመን ግራውንድ፤ ዘ ወተር፤ ኧርዝ፤ ኤንድ ኤየር ዊ ሼር (Common Ground: The Water, Earth, and Air We Share)**

*ደራሲ፤* ሞሊ ባንግ (Molly Bang)

**ይዘቶች (Themes)፤** አካባቢ እና ዘላቂነት (Environment and Sustainability)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤** ብዙ ሰዎች የጋራ ሪሶርሶችን የሚያገኙበት እና የዓለማችንን አካባቢ በአስተማማኝ ሁኔታ የመቆጣጠርን ተግባር የሚወያዩበትን መንደር በምናብዎ ያስቡ።

## ጮክ ብለው ያንብቡ (READ ALOUD)

**ከንባብ በፊት፤ መሰረት ይገንቡ (Build Background)**

- ልጅዎን “የፕላኔታችንን የተፈጥሮ ሃብቶች መንከባከብ ለምን አስፈላጊ ነው?፤ እና እነሱንስ በዕለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ እንዴት እንጠቀማለን?” በማለት ይጠይቁ።

**በንባብ ወቅት፤ ግንኙነቶችን ይፍጠሩ (Make Connections)**

- ደራሲው ታሪኩን በበግ ግጦሽ ታሪክ የጀመረው ለምን ይመስላችኋል?
- ውሃ፣ አየር እና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶችን ለመጋራት እያንዳንዱ ሰው ምን ማድረግ እንደሚችል ታሪኩ ምን ይነግረናል? ስለ ንግዶች እና እርሻዎችስ?
- በታሪኩ ውስጥ ፕላኔቶች እንዴት ተገልጸዋል? ከጽሁፉ ወይም ከሰእሎቹ ምስሌዎችን መስጠት ይችላሉ?

**ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ**

- በፕላኔቷ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የግለሰብ እና የቡድን ምርጫዎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ መስራት ይችላሉ? በግለሰቦች፣ ንግዶች እና እርሻዎች የሚጠቀሙባቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች ያካትቱ እና ሊጠበቁ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉባቸውን መንገዶች ይዘርዝሩ።

## ተዛማጅ ተግባራት

**ልጅዎ ይህን መጽሃፍ ከወደደ፤ የሚከተሉትን ከግምት ያስገቡ፤**

- በሌሎች ንግግሮች ጊዜ ስለ እሱ እንዲያወሩ አበረታቷቸው።
- በተዛማጅ መጽሃፍት እና ሪሶርሶች (resources) ስለ ዘላቂነት (sustainability) የበለጠ ለማወቅ የአር አይ ኤፍን (RIF’s) Sustainable Futures ማዕከልን ይመልከቱ።


©2024 Reading Is Fundamental